**ORIGINAL ARTICLE**

# Oral History and its Significance of Takle ʾAqʷāqʷām

**Addisie Yalew Mengistu [1]**

## *Abstract*

*This study is presented under the title of 'Oral History and its Significance of Takle ʾAqʷāqʷām. The objectives of the study are how the Takle ʾAqʷāqʷām was authored, how it was passed down from generation to generation, how the story looks over time, and the current status and importance of this Ethiopian Orthodox Tawāhdo church Swaying and Chanting. The study utilized purposive and simple random sampling methods for data collection by using observation, interviews, and analysis of primary and secondary documents. The study was analysed using descriptive and narrative methods from the qualitative data analysis method. The result of this study is that Takle ʾAqʷāqʷām (Swaying and Chanting) of the Ethiopian Orthodox Tawāhdo church was authored by ʾAlaqā Gabra Ḥanā (r.1821–1902) around Lake Tana region and then Gabra Ḥanā taught this newly invented ʾAqʷāqʷām to his son Takle (r.1860–1915). However, Takle went to Wallo for some reason. When the church Tantā Mikāʾel in Wallo was founded, Takle presented this ʾAqʷāqʷām. After he became known as the elite of this ʾAqʷāqʷām during that time, Rās Gugsā Wale (r.1875–1930) requested and got permission approval from Rās Mikāʾel of Wollo (r.1850–1918) for bringing Takle to Dabra Tābor ʾIyasus church. Then Rās Gugsā assigned him as the teacher of this newly invented Aqʷāqʷām and governor of the ancient Dabra Tābor ʾIyasus church. Takle taught this Aqʷāqʷām until he passed away which is also later named by his name. This Aqʷāqʷām well expanded in the country after the death of Takle where many church school teachers between Takle to the contemporary teacher Mamhər Maršā teach at Dabra Tābor ʾIyasus church. However, the continuation of this Aqʷāqʷām is in danger of extinction because the learning and teaching process is only through oral methods and it has not yet been published or filmed. Another problem is that there aren't any subordinate schools that could pre-train or subsidize students for this department. Thus, the study suggested that transcribing, publishing, and documentary filming of Takle Aqʷāqʷām is the first solution to preserve and transfer to the current and next generation. In addition, addressing the needs of the current attending students and the concerned parties should give the necessary attention to establishing the Takle ʾAqʷāqʷām as a heritage.*

**Keywords**: *Ethiopian Orthodox Tawāhdo church school and Takle 'Aqwaqwam*

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት የተክሌ አቋቋም ቃላዊ ታሪክ እና ፋይዳው በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። በዚህ መሰረት የተክሌ አቋቋም እንዴት እንደተደረሰ፣ ከትውልድ ትውልድ እንዴት እንደተላለፈ፣ በዘመናት ሂደት ውስጥ ታሪኩ ምን እንደሚመስል፤ አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ እና የተክሌ አቋቋም ትምህርቱን ጠቀሜታ ማሳየት የጥናቱ አላማ ነው። ይህን ከግብ ለማድረስ አላማ ተኮር እና እድል ሰጭ ናሙናን በመጠቀም በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ከተለያዩ ሰነዶች የተሰበሰቡ መረጃዎች ከዓይነታዊ መረጃ መተንተኛ መንገዶች ውስጥ በገላጭና ትረካዊ ስልት ተተንትነዋል። በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የተክሌ አቋቋም ባህላዊ ትምህርት በአለቃ ገብረ ሐና በጣና ሐይቅ አካባቢ እንደተደረሰ፤ ልጃቸውን ተክሌ ገብረ ሐናንም እንዳስተማሩ፣ ተክሌም ከአባቱ ያገኘውን ፈጠራ ይዞ ወሎ እንደሄደ፤ በወሎ ተንታ ሚካኤል ሲመረቅም አቋቋሙን እንዳቀረበው፤ ሊቅነቱ ከታወቀ በኋላ ንጉሥ ራስ ጉግሳ ወሌ ከወሎው ንጉሥ ራስ ሚካኤል አስፈቅደው ደብረታቦር ኢየሱስ እንዳመጡት ጥናቱ አሳይቷል። ራስ ጉግሳ ለተክሌ የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪነትና መሪጌትነት (ተክሌ አቋቋምን

1. University of Gondar, Department of Amharic Language and Literature
Email: yalewaddisie@gmail.com

የማስተማር ሀላፊነት) አንድ ላይ እንደሰጡት፤ ተክሌም እስከ እለተ ሞቱ ድረስ በደብረ ታቦር ኢየሱስ እንዳስተማረና ከእርሱ በኋላም የተለያዩ የተክሌ አቋቋም ሊቃውንት እያስተማሩ አሁን ካለው መምህር መርሻ መብራቱ እንዳደረሱት የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። የተክሌ አቋቋም ክዋኔ በአሁኑ ወቅት በመጥፋት ላይ እንደሆነና ለዚህም ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ጥናቱ አሳይቷል። ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ ሀሳቦች፡-የተክሌ አቋቋምን ይትበሀል (የማስተማር ሂደት) በመጽሐፍ በማሳተም የመማር ማስተማሩን ሂደት ምቹና ቀላል ማድረግ፤ የተክሌ አቋቋም ክዋኔውን በምስል (Documentary film) ቀርጾ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ፤ በተለያዩ ባህላዊ ትምህርት ቤቶች ለተክሌ አቋቋም ምንጭ የሚሆኑ ትምርት ቤቶች ማቋቋም፤ የተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላት እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ለተክሌ አቋቋም አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት በቅርስነት መጠበቅ የሚሉትን ጥናቱ ጠቁሟል።

**ቁልፍ ቃላት፡- ባህላዊ ትምህርት ቤት፣ ተክሌ አቋቋም**

## 1. መግቢያ

ስነቃል(Oral literature) የጽሑፍ ስልጣኔ ከመምጣቱ በፊትም ሆነ በኋላ የሰውልጅ ፍልስፍናውን፣አመለካከቱን፣እምነቱንና ታሪኩን የሚያንጸባርቅት የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነልቡናዊ፣ ፍልስፍና ወዘተ.የሚያሳይ ቃላዊ ሥነ ጽሑፍ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረትም ከስነቃል ዘርፎች ውስጥ በቃላዊ ተረክ ስር በሚካተቱት በግለሰባዊ ታሪክ (Personal narrative) እንዲሁም ቃላዊ ታሪክ (Oral History) ላይ ተመስርቶ ይቀርባል። ቃል ታሪክና ሌሎች የፎክሎር ዘርፎች ለታሪክ እንደ መረጃ ምንጭ የሚያገለግሉ ናቸው። በተለይ የመጻፍና የማንበብ ባህል የሌላቸውን ማኅበረሰቦች ታሪክ የምናዋቅረው ቃል ታሪክን እንደ ማሙያነት (source) እና እንደ ተሟሚይነት (complementary) በመጠቀም ነው (ዘሪሁን፣ 1992፣ Barbara Allen,1979) ። አንድ ግለ ተረክ ስለ አንድ ግለሰብ ቡድን ቤተሰብእ ወይም ማኅበረሰብ ታሪክ፣ ልዩ ገጠመኝና ልምድ የሚገልጽ የቃል ተረክ ዘርፍ ነው። ይህ የሚጠናበት የጥናት ዘርፍም ቃላዊ ታሪክ (Oral History) በመባል ይታወቃል (ሰሎሞን ፣2007፡114)። ይህ ጥናትም በተክሌ አቋቋም ቃላዊ ታሪክ ላይ የሚያተኩር ነው።

የተክሌ አቋቋም የኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካሏት ባህላዊ የትምህርት አይነቶች ውስጥ በአቋቋም ስር የሚካተት ነው። ካህናቱ ሀገረሰባዊ ልብስ ለብሰው በተለካ ድምጽ በእንቅስቃሴ የሚያቀርቡት ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ስለሆነ ከዜማ፣ ከዝማሜ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት አለው። የተክሌ አቋቋም ከማኅበረሰቡ ጋር ለረጅም ዘመናት አብሮ የቆየ ነው። ‹‹ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሊቁ አለቃ ገብረሐና የጀመሩት በልጃቸው አለቃ ተክሌ ስም የተክሌ አቋቋም በመባል እስከ አሁን ድረስ ይታወቃል። ካህናቱም በመሐል ሀገርና በሰሜን ኢትዮጵያ እስከ አሁን ድረስ ይጠቀሙበታል›› (መሰለ፣2006፡37-38)።

በአሁኑ ጊዜ በደብረ ታቦር ከተማ የሚገኘው የደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ብቸኛ የተክሌ አቋቋም የምስክር ማረጋገጫ ማዕከል ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። የተክሌ አቋቋምን ጨምሮ ባህላዊ ትምህርት ቤቶች በማኅበረሰቡ የተለያየ ስያሜ አላቸው ለምሳሌ የቄስ፣የቆሎ፣ የአብነት፣ የመድረሳ (በእስልምና) ትምህርት ቤት እየተባሉ ይጠራሉ።

ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት የሆነው የተክሌ አቋቋም ክዋኔው በመጥፋት ላይ ይገኛል። ለመጥፋቱ አንዱ ምክንያት የአቋቋሙ የትመጣነት፣ ምንነትና ጠቀሜታ በሰፊው አለመታወቅ ነው። እኔንም ይህን ጥናት እንዳካሂድ ካነሳሳኝ ምክንያት አንዱ የተክሌ አቋቋምን የመጥፋት ሁኔታ በቅርበት የተረዳሁ መሆኔና የዚህ ሀገር በቀል እውቀትና ቅርስ መጥፋት ስለሚያሳስበኝ ይህን አጥንቶ ለማኅበረሰቡ በማሳወቅ ማኅበረሰቡ የበኩሉን እንዲወጣ ለማድረግ እና እኔም የድርሻየን ለመወጣት ነው። በተጨማሪም ከዚህ በፊት በተክሌ አቋቋም ታሪክ ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይንሳዊ ጥናት ተሰርቶ ባለማግኘቴ ታሪኩን አጥንቶ ለማሳወቅና ጠቀሜታውን ለማሳየት ተጠንቷል። እንዲሁም ከዚህ በፊት በተሰሩ መጣጥፎች ውስጥ የተክሌ አቋቋምን ራሱን ችሎ ያቀረበ ሰው የለም። የአብዛኛዎቹ ጽሑፎች ትኩረት የአለቃ ገብረሐና ህያውነት፣ ሊቅነትና ቀልደኛነት ትኩረት ያደረገ ነበር። ስለዚህ ይህ ጥናት ካለፉት ስራዎች የሚለየው፡- ስለተክሌ

አቋቋም በሳይንሳዊ መንገድ የተብራራ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ስራ ትንታኔ ያቀረበ በመሆኑ፣ ተክሌ አቋቋም ከተደረሰበት ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ዘመናት የነበረውን ታሪክ አዋቅሮ ማሳየቱ ፣ የተክሌ አቋቋም በመከወኑ ለማኅበረሰቡ ያለውን ጠቀሜታ ማብራራቱ፣ ተክሌ አቋቋም አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ መግለጹ፣ የተክሌ አቋቋምን ጠብቆ ለማቆየት መደረግ ያለባቸውን የመፍትሔ እርምጃዎች መጠቆሙ ናቸው፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና አላማ የተክሌ አቋቋምን ቃላዊ ታሪክ፣ አሁን ያለበትን ሁኔታና ፋይዳውን መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

- የተክሌ አቋቋም መቸ፣ የት፣ በማን እንደተደረሰ መግለጽ፡፡
- የተክሌ አቋቋም መቸ፣ የት፣ በማን እንደተጀመረ ማብራራት፡፡
- የተክሌ አቋቋም በየዘመናቱ የነበረውን ታሪክ በቅኝት ማሳየት፡፡
- የተክሌ አቋቋም ትምህርት ለማኅበረሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ ማብራራት፡፡

ባህላዊ ትምህርቶች ቢጠኑ ለማኅበረሰቡ የሚያበረክቱት የራሳቸው የሆነ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡ ፡ ይህ ጥናትም የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል፡፡ ስለ ተክሌ አቋቋም አደራረስ፣ አጀማመር፣ የዘመናት ታሪክ እና አሁን ያለበትን ሁኔታ ያሳያል፤ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ተመስርቶ ለሚጠና የኢትዮጵያ ታሪክ መረጃ ሰጭ ይሆናል፣ የተክሌ አቋቋም ድርሰት ለማኅበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ይገልጻል በተጨማሪም ወደፊት ከዚህ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናት ለሚያደርጉ ባለሙያዎች መረጃ ይሰጣል፡፡ በአጠቃለይ ስለ ተክሌ አቋቋም አደራረስ፣ አጀማመር፣ የዘመናት ታሪክ፣ አሁን ያለበትን ሁኔታና ለወደፊት መወሰድ ያለባቸው የመፍትሔ እርምጃዎችን ያብራራል፡፡

ይህ ጥናት ከባህላዊ ትምህርቶች ውስጥ በተክሌ አቋቋምና በዚህ አቋቋም ደራሲ ቃላዊ ታሪክ የተወሰነ ነው፡፡ ከላይ በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት እንደተገለጸው ቅርሱ በመጥፋት ላይ ስለሚገኝና ከዚህ በፊት ራሱን ችሎ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ያልተጠና በመሆኑ ሲሆን ለጥናቱ ቦታ ደቡብ ጎንደር የተመረጠውም ደቡብ ጎንደር ዞን የተክሌ አቋቋም የተደረሰበትና መረጃው ያለበት ፣እስከአሁን ትምህርቱ የሚሰጥበት፣ ታሪኩ የሚታወቅበት፣ የተክሌ አቋቋም ሊቃውንት ያሉበት፣ የደራሲው የአለቃ ገብረሐና የትውልድ ሀረጎች የሚገኙበት ስለሆነ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ሲባል ይህ ቦታ ተመርጧል፡፡

## 2. የአጠናን ዘዴ

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ ሰዎች በተክሌ አቋቋም ዙሪያ ለሚነገሩ ቃል ታሪኮች ያላቸው ቅርበት፣እውቀት፣ልምድና የአገላለጽ ብቃት ይለያያል:: በመሆኑም አላማ ተኮርና እድል ሰጭ ናሙናን መሰረት በማድረግ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ የታመነባቸው የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰቦች መረጃ ሰጭ ሁነው ተመርጠዋል፡፡እነዚህም፡-

- የተክሌ አቋቋም ትምህርትን ወንበር ዘርግተው የሚያስተምሩ የማረጋገጫ ምስክር የሚሰጡ ሊቃውንት፡፡
- ስለተክሌ አቋቋም ትምህርት የሚያውቁ መርጌታዎችና እንዲሁም ካህናት
- የተክሌ አቋቋም ዝማሜን የሚያውቁ በቤተክርስቲያን በበዓላት የሚታደሙ የደቡብ ጎንደር ማኅበረሰብ አባላት፡፡

- በባህላዊ ትምህርት ቤት ውስጥ ስለ ተክሌ እና ባህላዊ ትምህርት ታሪክ የሚያውቁ የመጻሕፍት መምህራን፡፡

- የተክሌ አቋቋምን በመማር ላይ ያሉ የአብነት ተማሪዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡በተጨማሪም ካልዓይ መረጃዎች ከመጣጥፎች ተሰብሰበዋል፡፡

ከነዚህ የመረጃ ምንጮች መረጃዎች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና እንዲሁም ከመረጃ መሰብሰቢያ ቁሳቁስ አንጻር በማስታወሻ ደብተር፣ በመቅረጸ ምስልና እና ድምጽ ተሰብስበዋል፡፡

ምልከታ አንድ ሀገረሰባዊ እውቀት በክዋኔ መልክ በሚቀርብበት ጊዜና ቦታ በመገኘት መረጃ በሁሉም የስሜት ህዋሳቶቻችን የምንሰበስብበት ሂደት ነው፡፡ በምልከታየም የተክሌ አቋቋምን የደብረታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የማትጠቀምበት ጊዜ እንደሌለ አስተውያለሁ፡፡ በተለይ በበዓላት፡- የልደት ታህሳስ 29 ፣መጋቢት 29፣ የእርገት ፣የደብረ ታቦር ነሐሴ 13፣ በዐቢይ ፆም ማህሌት ላይ በመገኘት ተመልክቻለሁ፡፡ በእነዚህ ዐበይት በዓላት ሊቃውንቱ በብዛት የሚገኙበት ስለሆነ እንዲሁም ደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንና በቅኔ ምሽት ላይ የተክሌ ሊቃውንት የተክሌ ዝማሜን ሲያቀርቡ ጠቃሚ ጉዳዮችን ለመመልከት ችያለሁ፡፡

ስለ ቃለ መጠይቅ ያለው ‹‹ተመራማሪው ቃለመጠይቅን እንደመረጃ መሰብሰቢያነት ለመጠቀም ከወሰነ ከሚከተሉት የቃለመጠይቅ አይነቶች በአንዱ፣ በሁለቱ ወይም በሁሉም መጠቀም ይችላል፡፡እነሱም ውስን ቃለ መጠይቅ፣ ከፊል ነጻ ቃለመጠይቅና ነጻ ቃ ለመጠይቅ ናቸው ›› ይላል (ያለው፣1998፡113) ፡ ፡ በዚህ ጥናትም ከፊል ነጻ ቃለመጠይቅን በመጠቀም ለመረጃ ሰጭዎች የሚጠናውን ችግር ካስተዋወኩ በኋላ መረጃ ሰጭዎች ነጻነት በተሞላበት መንገድ እውቀታቸውን፣ አስተያየታቸውን እና አመለካከታቸውን እንዲገልጹ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ስለሆነም አላማ ተኮር ናሙናን መሰረት በማደረግ ሰባት ዋና መረጃ ሰጭዎችንና እንዲሁም በእድል ሰጭ ናሙና አስራ አምስት ንዑስ መረጃ ሰጭዎችን ቃለመጠይቅ አድርጌአለሁ፡፡ እነዚህም ስለተክሌ አቋቋም የሚያውቁ የመጻሕፍት መምህራን፣የተክሌ አቋቋም መምህራን፣የተክሌ አቋቋም ተማሪዎች በማህርሰቡ የተመሰከረላቸው ታሪክ አዋቂዎች እና በተክሌ አቋቋም የሚገለገሉ ማህበረሰቦች ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ከዚህ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መጣጥፎችን በመፈለግ ከርዕሱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ለይቶ በማውጣት ለማስረጃነት በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡ይህ ጥናት በአይነታዊ የምርምር ስልት ስር የሚካተት ሲሆን በትንተናው ሂደት በመጀመሪያ ከመስክ በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተገኙ እና እንዲሁም ከመጣጥፍ የተሰበሰቡ መረጃዎች ባላቸው የጭብጥ ግንኙነት መሰረት እየተመደቡ ተተንትነዋል፡፡ በተጨማሪም ቀደም ሲል የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች ከተለያዩ ዳራዎች ጋር በማገናዘብ ገላጭ እና ትረካዊ መተንተኛ ስልትን ተከትለው ተተንትነዋል፡፡

## 3. የመረጃ ትንተና

### 3.1. የተክሌ አቋቋም አደራረስ ታሪክ

ስለ ተክሌ አቋቋም አደራረስ የተለያዩ መላምቶች ይነሳሉ፡፡ ይኸውም ተክሌ አቋቋም በባህታዊ ጸዓዳ ገብረ ስላሴ በጣና ሀይቅ ሬማ መድኃኔዓለም ተደረሰ፤ በአለቃ ገብረሐና በጣና ሀይቅ ዳርቻ በናበጋ፣በዘጌ ተደረሰ እና በሬማ መድኃኔዓለም በአለቃ ገብረሐናና በጸዓዳ ገብረ ስላሴ ተደረሰ የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የተነሱ ሀሳቦችን እንመለከት፡-

> አለቃ ገብረሐና በብዙ ሙያዎች የተካኑ ባለቅኔ፣ የአቡሻክር እና የመረሀ እውር ሊቅ፣ የድጓ ምሁር፣ የፍትሐ ነገሥት ሊቅ፣ የአቋቋም አዋቂ፣ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህር ነበሩ፡ ፡ መቸም ለዚህ ለዝማሜ እሚባለው ለመቋሚያ እገሌ ይመስለዋል አይባልም ከገብረሐና

> ፊት የሚዘም የለም። አለቃ ገብረ ሐና ለቤተክርስቲያን እና ለኢትዮጵያ ካበረከቱት ነገር አንዱ የተክሌ ዝማሜ የሚባለው ነው። ገብረሐና ይህንን የመቋሚያ ስልት ያዘጋጁት ከአጼ ቴዎድሮስ ሸሽተው ዘጌ በገቡ ጊዜ ነበር በዚያ የነበረውን የሸንበቆ ውዝዋዜ ተመልክተው ከአቋቋሙ ስልት ጋር አዋህደው ከባህታዊ ጸዓዳ ገብረ ስላሴ ጋር በመሆን ነበር ያዘጋጁት ባህታዊ ጸኣዳ ገብረ ስላሴ ወደ ዓለም ስላልተመለሱ አለቃ ገብረሐና ይህን አዲስ ዝማሜ ይዘው ጎንደር ገቡ። ወዲያውም የአቋቋሙ መምህር አለቃ ገብረሐና ለተማሪዎቻቸው አዲሱን ዝማሜ ማስተማር ጀመሩ (ዳንኤል ክብረት፣2009)።

አለቃ ገብረሐና ሬማ መድኃኔዓለም በገቡ ጊዜ ጸዐዳ ሚካኤል የሚባሉ ባህታዊ አገኙ ባህታዊውም መላከ እግዚአብሔር እያናጋራቸው የተክሌ አቋቋምን ደረሱ ከዚያም ጸዓዳ ሚካኤል በዚያው ይህን ትምህርት ለአለቃ ገብረ ሐና አስተማሯቸው ጸዓዳ ሚካኤልም እኔ ወደ ዓለም አልወጣም አንተ ሂድና አስተምር አሏቸው አለቃ ገብረሐናም ይህን አዲስ አቋቋም ይዘው ጎንደር ገቡ (ቃለ መጠየቅ፣መላከታቦር ኃይለ ኢየሱስ፣ 21/07/2010)። ሁሉን ፊት ለፊት የሚናገሩት አለቃ ገብረሐና ለአጼ ቴዎድሮስ ፍትሐ ነገሥቱን የሚፈቱ ምሁር ነበሩ።ነገር ግን ንጉሡ በካህናት ቁጥር ቅነሳ ላይ ያደረጉትን ደጋግመው በመንቀፋቸው አጼ ቴዎድሮስ ገብረ ሐና እኔ ከማልገዛው ሀገር ሂድ ብለው ትዕዛዝ ሰጧቸው። በዚህ ጊዜ ጣና ሐይቅ ሬማ መድኃኔዓለም ሱባኤ ገቡ በዚያም ሲጸልዩ ሲጸልዩ የተክሌ አቋቋምን መላከ እግዚአብሔር ገለጠላቸው (ቃመ. ርዕሰ መምህራን መርሻ ፣08/09/2010) ።

‹‹አለቃ ገብረሐና በጣና ሃይቅ ሱባኤ ገብተው ሳለ መላከ እግዚአብሔር ተገልጦ የተክሌ አቋቋምን ነገራቸው ። አለቃ ግን መልሰው እንዴት ይህን ላደርግ ይቻለኛል ብለው መላኩን ጠየቁት መላኩም ሂድና የነገርኩህን ያገርህን ሸምበቆ እያየህ አዘጋጀው አሏቸው። አለቃም ሸንበቆውን እያዩ ተክሌ አቋቋምን ደረሱት›› (ቃመ. መሪ ጌታ ዘውዴ፣ 08/09/2010)።

የተክሌ አቋቋም አደራረስን በተመለከተ ከተለያዩ ምሁራን መጻሕፍት የተገኙ ሀሳቦች ደግሞ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

> አረፈ አለቃ ገብረ ሐና ከጣና ሀይቅ በስተምስራቅ የሚገኘው የፎገራ ተወላጅ እንደመሆናቸው ህይወታቸው በብዙ መንገድ ከሐይቁ ጋር የተቆራኘ ነበር አለቃ ከዕለታት በአንድ ቀን ጣና ሀይቅ ዳርቻ አረፍ ብለው ሳለም አስገራሚ ትሪዒት አዩ የሀይቁ ሞገድ በአካባቢው የሚገኙትን ሸንበቆዎች እያዘመመ ልክ ጣዕመ ዜማ እንደተቀመረላቸው ዳንኪራዎች አንዴ ወደ ግራ ቀጥሎም ወደ ቀኝ ሲያዘናፍላቸው ተመለከቱ የሰው ልጅም በዚህ መልክ ሊወዛወዝ የተገባ ነው ብለው አዲስ የዝማሬ ትምህርትን ፈለሰፉ ይላሉ (አረፈ አይኔ፣ 1979፡34)።

አጼ ቴዎድሮስ አለቃ ገብረሐና ታድነው እንዲያዙ ትእዛዝ ሰጡ በዚህ መንስኤ አለቃ ገብረ ሐና ሸሽተው ጣና ሀይቅ ገብተው ለጥቂት አመታት ተደብቀው ነበር። ሊቁ አለቃ ገብረሐና ዘጌ ደሴት ውስጥ እንዳሉ ነበር የውሃ የውቅያኖስ ነፋስ ወይንም ማዕበል (wave) ተነስቶ የአካባቢውን ሸንበቆ ግራና ቀኝ ሲያወዛወዘው የተመለከቱት የሰው ልጅም በዝማሜ እንዲህ መዝመም ይችላል ብለው ማሰላሰል ጀመሩ ከዚያም እዚያው ጣና ሀይቅ ውስጥ ከሚገኘው ሬማ መድኃኔዓለም ገብተው ባህታዊ ጸዓዳ ገብረ ስላሴ ከሚባሉ የአቋቋም ሊቅ ጋር ሆነው የተፈጥሮ አስተውሎታቸው ውጤት የሆነውን አዲሱን ዝማሜ በወጉ አዘጋጁት(መሰለ፣ 2006፡ 59)።

በተለያዩ መጣጥፎች እና መረጃ አቀባዮች እንደተገለጸው የተክሌ አቋቋም ድርሰት ከአለቃ ገብረሐና የሸንበቆ ውዝዋዜ የተፈጥሮ አስተውሎት አንደተገኘ ሲገልጹ አንዳንዶቹ ደግሞ ባህታዊ ጸዓዳ ገብረ ስላሴ (ገብረ ሚካኤል) ጋር በመሆን እንደደረሱት ይናገራሉ። አቋቋሙ የተደረሰበትን ቦታም ሬማ መድኃኔዓለም፣ ዘጌ፣ ናበጋ በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች የተገለጸ ሲሆን እንዚህ ሁሉ በጣና ሃይቅ ውስጥና ዙሪያ የሚገኙ በመሆናቸው ተክሌ አቋቋም በጣና ሃይቅ አካባቢ ተደረሰ ብሎ መደምደም ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ

በሁሉም ትረካዎች ተክሌ አቋቋምን ለመጀመሪያ ጊዜ በጎንደር ያስተዋወቁት አለቃ ገብረሐና መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ከዚህ በመነሳትም የተክሌ አቋቋም ደራሲና ቀማሪ በፎገራ ወረዳ በናበጋ ጊዮርጊስ በ1814 የተወለዱት በአብዛኛው ሰው ዘንድ በቀልዳቸው ብቻ የሚነሱት ነገርግን ባለቅኔ፣ የአቡሻክር እና የመረሀ እውር ሊቅ የድጓ ምሁር፣ የፍትሐ ነገሥት ሊቅ፣ የአቋቋም አዋቂ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህር የነበሩት አለቃ ገብረሐና ደስታ ተገኝ ናቸው፡፡ ከመረጃዎች በመነሳትም አለቃ ገብረሐና ከአጼ ቴዎድሮስ ጀምሮ እስከ አጼ ሚኒሊክ ዘመን በነበሩት ነገሥታት በቤተ መንግሥት የፍትሐ ነገሥት ተርጓሚና ፍርድ ሰጭ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን ተክሌ አቋቋምን ጣና ሃይቅ አካባቢ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የደረሱ ሰው ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡



ከድረ ገጽ የተገኘ የአለቃ ገብረሐና ደስታ ተገኝ ፎቶ 1814-1898 ዓ.ም www.danielkibret.com

ዳንኤል (2009) ይህን ፎቶ አስመልክቶ ‹‹አለቃ ገብረ ሐና ፎቶአቸው ለትውልድ ከተቀመጠላቸው ጥቂት የጥንት ሊቃውንት አንዱ ናቸው፡፡ በ1890 ዓ.ም ሙሴ ሜንሮስ የተባለ ጣልያናዊ ያነሣቸው ፎቶ ግራፍ እና አንድ እስካሁን ፎቶ አንሺውን ማወቅ ያልቻልኩት በኢንተርኔት የተለቀቀ ፎቶ ግራፍ አግኝቻለሁ›› ይላል፡፡

## 3.2. የተክሌ አቋቋም አጀማመር

አለቃ ገብረ ሐና የተክሌ አቋቋምን ይዘው ጎንደር ከገቡ በኋላ አዲሱን ፈጠራ ለሊቃውንቱ ማስተማር ጀመሩ ይሁን እንጅ አቋቋሙ ለሊቃወንቱ አዲስና የለበሱትን ሸማ እያስጣለ የሚያስቸግር በመሆኑ ተቀባይነትን አላገኘም ነበር፡፡ አለቃ ገብረሐናም ይህን አዲስ ፈጠራ ለትውልድ ሳያስተላልፉ ማለፍ ስላልፈለጉ ልጃቸው ተክሌን ደብቀው አስተማሩት ተክሌም ከሌላ የቤተክርስቲያን እውቀቱ ላይ አዲሱ ፈጠራ ሲጨመርለት የታወቀ ምሁር ሆነ፡፡

ተክሌ ወሎ ተንታ ሚካኤል ሲመረቅ ያንን ተደብቆ የኖረ ዝማሜውን አወጣው መኳንንቱ እና መሳፍንቱ፣ ህዝቡ እና ካህናቱ ተገርመው ያዳምጡት እና ያዩት ጀመር ሲጨርስም ራስ ሚካኤል በተንታ ሚካኤል ይህንን ዝማሜ እደንዲያስተምር አደረጉ በኋላም የደብረ ታቦሩ ራስ ጉግሳ ራስ ሚካኤልን አስፈቅደው ለደብረ ታቦር ኢየሱስ አለቃ አድርገው ተክሌን ወሰዱት እርሱም በዚያ ሲያስተምር ቆይቶ እዚያው አረፈ ዝማሜውም በስሙ ተክሌ አቋቋም ተባለ ይላሉ (ዳንኤል፣2009)፡፡

ራስ ሚካኤል ጋር እንዲኖር ያደረጉት ልጃቸው ተክሌ እጅግ በላቀ የክህነት አገልግሎት ዝናና ግነትን ስላገኘ ራስ ጉግሳ ወደ ደብረ ታቦር እንዲመጣ አድርገውት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለቃ ሆኖ ትምህርት ቤት ከፍቶ አባቱ የፈጠሩትን አቋቋምንና የአቋቋም ተግባራትን ዝማሜን፣ቁምን፣መርግድን፣ጽፋትን፣በገሀድ ማስተማር ጀመረ፡፡ በምዕመናንና በካህናቱ ዘንድም አድናቆትን ተጎናጸፈ ከአምባ አምባም፣ ከደብር ደብርም ታውቆበት ይህን አዲስ አቋቋም አስፋፋው (መሰለ፣2006፡62፣74፣75)፡፡


> የአለቃ ገብረ ሐና ልጅ አለቃ ተክሌም እንደ አባታቻው የላይ ቤትና የታች ቤት አቋቋምን ጠንቅቀው የሚያውቁ በወቅቱ ከነበሩ እውቅ ምሁራን አንዱ ከመሆናቸው ባሻገር አባታቸው በጣዕመ ዝማሬ ዘመላዕክት የቀመሙትን ዝማሜ የሌሊት እረፍታቸው መስዋዕት በማድረግ የተማሩ ይህንኑ አባታቸው ያወረሷቸውን ዝማሜ እንዳጠናቀቁ ከመንፈሳዊ መሪ ራስ ጉግሳ ወሌ ጋር ተገናኙ እሳቸውም እውቀታቸውንና ማንነታቸውን ጠይቀው ከተረዱ በኋላ የደብረ ታቦር ኢየሱስ አለቃ አድርገው ሾሟቸው፡፡ ተክሌም በዚህ አጋጣሚ ቀድሞ የነበራቸውን ደቀ መዛሙርት ከያሉበት ሰብስበው የተክሌውን ዝማሜ ለማስተማርና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማዋል ችለዋል (ቤተ ማሪያም፣1989፡1)፡፡

ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ትንተና የሚከተሉት ናቸው፡፡

2ኛው ራስ ጉግሳ ወሌ በዘመኑ የደብረ ታቦር ንጉሥ የነበሩት ደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን አፍርሰው በአዲስ መልክ በ1894 አሰሩ፡፡ ራስ ጉግሳ ቤተ ክርስቲያኑን አሰርተው እንደጨረሱ ወደ ቦታው ለማምጣት ሊቃውንትን ይመለምሉ ነበር፡፡ ስለሆነም ከወሎ ራስ ሚካኤል ዘንድ አለቃ ተክሌን አስፈቅደው አመጧቸው፡፡ ተክሌም በደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ወንበር ዘርግተው ማስተማር ጀመሩ (ቃመ.ቀኝ ጌታ አዳነ፣03/09/2010)፡፡

‹‹የተክሌ አቋቋምን አለቃ ገብረሐና ጎንደር ሲያስተምሩ ተቀባይነት አላገኙም ስለሆነም ከራሳቸው እና ከልጃቸው ተደብቆ የኖረው ተክሌ አቋቋም ተቀባይነት አግኝቶ ጉባኤ ቤት ተዘርግቶ በራስ ጉግሳ ወሌ መልካም ፈቃደኝነት የተጀመረው ደብረ ታቦር ኢየሱስ ነው፡፡›› (ቃመ. መላከ ታቦር ኃይለ ኢየሱስ፣ 21/12/2010)

ከጽሑፍ እና ከቃል የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የተክሌ አቋቋም የተጀመረው በራሳቸው በአለቃ ገብረሐና በጎንደር ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ትምህርቱ በምሁራን ዘንድ ተቀባይነት ባለማገኘቱ በአለቃ ገብረሐና እና በልጃቸው አለቃ ተክሌ ብቻ ተደብቆ የቆየ መሆኑን ከመረጃዎቹ እንረዳለን፡፡ አለቃ ገብረሐናም አቋቋሙን ለልጃቸው ብቻ ማስተማራቸው በሌሎች የቤተክርስቲያን ምሁራን ዘንድ ተቀባይነት ባለማግኘታቸው እውቀታቸውን ይዘው ማለፍ ስላልፈለጉ የተጠቀሙት የመጨረሻ አማራጭ መሆኑን ጥናቱ አትቷል፡፡ወደ ንጉሥ ሚካኤል ዘንድ ተክሌን የላኩበት ሌላው ምክንያትም ልጃቸው እውቀቱን ለትውልድ ሳያስተላልፍ በድርቡሽ እንዳይገደል መሆኑን እንረዳለን፡፡ አለቃ ተክሌም በወሎ በተፈጠረለት አጋጣሚ አቋቋሙን ለንጉሥ ሚካኤል አቅርቦ በዚያ ተክሌ አቋቋም እንደተጀመረ እንረዳለን፡፡ ስለዚህ ተክሌ አቋቋም በጎንደር ቢጀመርም ተቀባይነት ባለማገኘቱ፤ ተቀባይነት አግኝቶ የተጀመረው በወሎ ተንታ ሚካኤል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ተቋማዊ እና ምስክር (እውቅና) የሚሰጥበት ጉባኤ ትምህርት ቤት ሆኖ በዋናነት የተጀመረው ደግሞ 1894 በደብረ ታቦር ኢየሱስ መሆኑን የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ ይኸውም ተክሌ በ2ኛው ራስ ጉግሳ ወሌ አማካኝነት ወደ ደብረ ታቦር ከመጣ በኋላ ወንበር ዘርግቶ ማስተማር የጀመረው በዚሁ ቦታ በመሆኑ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ ትምህርቱ የተለያዩ አይነቶች ኖረውት፤ ዝማሜን፣ቁምን፣መርግድን፣ጽፋትን፣ ማስተማር የጀመረው በዚሁ በደብረ ታቦር ኢየሱስ ነው፡፡ አሁን ድረስም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብቸኛ የምስክር ማረጋገጫ ማዕከል ሆኖ የሚሰጥበት ይኸው ደብረ ታቦር ኢየሱስ መሆኑን በጥናቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡



ከደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የተገኘ አለቃ ገብረ ሐና ተክሌን ደብቀው ሲያስተምሩት የሚያሳይ ስዕል (ፎቶ 29/10/2010)

3.3. የተክሌ አቋቋም ታሪክ በየዘመናቱ

በመጀመሪያው ዘመን የተክሌ አቋቋም በዋናነት ተቋማዊ ሆኖና ጉባኤ ተዘርግቶ ትምህርቱ የተጀመረበት እና የተስፋፋበት፣ከአምባ አምባ ከአገር አገር ታሪኩ የተነገረበት በመሆኑ በተክሌ አቋቋም ታሪክ ‹‹ ወርቃማ ዘመን›› መሆኑን ከቃልና ከጽሑፍ የመረጃ ምንጮች መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ ዘመን ተክሌ አቋቋም እየተስፋፋ እያለ አስተማሪው አለቃ ተክሌ በሞሞታቸው የተነሳ ንጉሡ ራስ ጉግሳና የአካባቢው ማኅበረሰብ እጅግ እንዳዘኑ ከገለጻዎች መረዳት ይቻላል፡፡

በሞተ ጊዜም፡-

‹‹ተክሌ ገብረ ሐና ተከተተ ጣቱ

መንክረ ከሰተን የዘመመበቱ›› ብላ አልቃሽ ገጥማ ነበር ፡፡ራስ ጉግሳም ምን ተክሌ ሞተ ትሉኛላችሁ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ፈረሰ በሉኝ እንጅ ፤ደብረ ታቦር ኢየሱስ ቢፈርስ ከዚህ አስበልጫ እሰራው ነበር ተክሌን ግን ከየት አገኝዋለሁ አሉ (ዳንኤል፣2009)፡፡ ‹‹ራስ ጉግሳ አለቃ ተክሌን ወደ ደብረ ታቦር እንዲመጣ አድርገውት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለቃ ሆኖ ጉባኤ ዘርግቶ አባቱ የፈጠሩትን አቋቋምንና የአቋቋም ተግባራትን ዝማሜን፣ቁምን፣መርግድን፣ጽፋትን፣በገሀድ ማስተማር ጀመረ በምዕመናንና በካህናቱ ዘንድም አድናቆትን ተጎናጸፈ ከአምባ አምባም፣ ከደብር ደብርም ታውቆበት ይህን አዲስ አቋቋም አስፋፋው›› (መሰለ፣2006፡ 74-74)፡፡

> የተክሌ አቋቋም ትምህርት በጣም ከመወደዱና ከመስፋፋቱ ጋር ዝናውም በየሀገሩ ስለወጣ ብዙ ደቀ መዛሙርት ወደ ደብረ ታቦር ኢሱስ ጎረፉ፡፡ ደብረ ታቦር ኢየሱስንም የተክሌ ዝማሜ መዲና ለመባል አበቋት፡፡ አለቃ ተክሌም ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ በማዞር ከዜማ ስልት ጋር እየስተባበሩና እየመሩ ከደቀመዛሙርቶቻቸው ጋር ቤተ ክርስቲያን ሲዘሙ

> የሚያይዋቸው የራስ ጉግሳ አይኖች ከላያቸው አልነሳ አሉ። እጅግ ተወደዱ ተከበሩ ታይተው የማይጠገቡ ሆኑ። ከአለቃ ተክሌ ጉባኤ የተክሌን ዝማሜ ሲማሩ የነበሩ ብዙ ቢሆኑም ከራሳቸው አልፈው ለሌላው ማስተማር ይችላሉ ብለው የመሰከሩላቸው እና እንዲየስተምሩ የፈቀዱላቸው እውቅ ደቀመዛሙርት የሚከተሉት ናቸው። አለቃ ብሬ፣ አለቃ መኮነን፣ አለቃ አለሙ ሰቆጤው እና አለቃ ይትባረክ ነበሩ (ጥዑመ ልሳን፣1981፡255)።

‹‹በ1894 ዓ.ም 2ኛው ራስ ጉግሳ ወሌ በዘመኑ የደብረ ታቦር ንጉሥ የነበሩት አለቃ ተክሌን ከወሎ አምጥተው እንዲያስተምር አደረጉ ተክሌም ጉባኤውን አስፍቶና አድምቆ እስከ ዕለተ ሞቱ ድርስ ወንበር ዘርግቶ በደብረ ታቦር ኢየሱስ አስተማረ›› (ቃመ.ቀኝ ጌታ አዳነ፣03/09/11)።

> በደብረ ታቦር ኢየሱስ አለቃ ተክሌ ለሶስት አመታት ያስተማሩ ሲሆን ትምህርታቸውም ከአድማስ አድማስ የተሰማበት ብዙ ሰው ወደ ጉባኤቸው የሚጎርፍበት ዘመን ነበር። ነገር ግን በቀራቸው እድሜ ያላቸውን እውቀት አስተምረው እንደማይጨርሱ በራዕይ ስለተነገራቸው ሶስት ሰዎችን መርጠው አንዱን ቅንዋቱን፣አንዱን መዝሙሩን፣አንዱን ክብሪ በዓሉን በማስተማር እና እርስ በርሳቸው መምህርና ተማሪ ሆነው እንዲማማሩ በማድረግ በዚህ ጥበብ የተክሌ አቋቋም ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ አድርገዋል። ከዚያም እነዚህ ሶስት ሰዎች እርስ በርሳቸው ተማምረው ተክሌ አቋቋም በነበረት ቀጥሏል። (ቃመ.መላከ ታቦር ኃይለ ኢየሱስ፣21/07/2007)

ከመረጃዎቹ እንደምንረዳው የደብረ ታቦር  አስተዳዳሪ በነበሩት ራስ ጉግሳ ወሌ አማካኝነት ተክሌም በደብረ ታቦር  ኢየሱስ ወንበር ዘርግቶ ሲያስተምር ትምህርቱ በብዙ ቦታዎች እንደተስፋፋ እንረዳለን።በዚህ ዘመን አለቃ ገብረሐና በጎንደር እንደገጠማቸው ተክሌ አቋቋም በሊቃውንት ተቀባይነት አላጣም በንጉሡም በህብረተሰቡም ዘንድ ተቀባይነትን አገኘ፤ በወሎ እንደነበረው ተንታ ሚካኤል ሲመረቅ ብቻ የሚቀርብ አልሆነም ይልቁንስ መደበኛ ትምህርት ተከፍቶ ሊቃውንት የሚያጠኑት በአጭር ጊዜ የተስፋፋ ትምህርት ሆነ። ከዚህ የተነሳም በተክሌ አቋቋም ታሪክ ይህ ዘመን ወርቃማ ዘመን ነው ማለት ይቻላል። ትምህርቱ ቢስፋፋም እንኳን በህይወት ብዙ ዓመት  እንደማይቆይ የተረዳው አለቃ ተክሌ አቋቋሙን ለትውልድ ለማስተላለፍ ሲል ለሶስት ሰዎች ሶስት የተለያየ ትምህርት በማስተማር የተክሌ አቋቋም ከትውልድ ትውልድ በማስተላለፍ ዘመን ተሸጋሪ እንዲሆን አድርጓል ማለት ይቻላል።




**የተክሌ አቋቋም ሊቃውንት የተክሌ አቋቋምን ሲዘሙ ከደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የተገኘ** (ፎቶ 29/10/2010)

የመካከለኛው ዘመን አለቃ ተክሌ ከሞተበት 1907 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ሲሆን ይህ ዘመንም በተክሌ አቋቋም ታሪክ ውስጥ ሁለተኛው ወርቃማ ዘመን ነው ማለት ይቻላል፡፡

> አለቃ ተክሌ አስተምሬው ሌላውን ያስተምራሉ ብለው የመሰከሩላቸውና የፈቀዱላቸው ቀጣይ የተክሌ አቋቋም ሊቃውንትም አለቃ ብሬ፣አለቃ መኮነን፣ አለቃ አለሙ፣ አለቃ ይትባረክ ናቸው ፡፡አለቃ ተክሌ ከሞቱ በኋላ ራስ ጉግሳ አለቃ ተክሌን የሚተካ ሊቅ ማን መሆን እንደሚገባው ቢጠይቁ አስተማሪ የነበሩት አለቃ ብሬ ራሳቸውን ትተው አለቃ መኮነን ጠቆሙ አለቃ መኮነን ከአገራቸው ከላስታ መጥተው በአለቃ ተክሌ ቦታ እንዲተኩ ተደረገ… ሆኖም አለቃ ብሬና አለቃ መኮነን በዝማሜ ቀለም (በተክሌ) አቋቋም ይትባህል ተጋጩ፡፡ ምክንያቱም አለቃ መኮነን ተክሌ በሞተበት ጊዜ ጎንደር ሄደው የጎንደሬን አቋቋም ተምረው ስለነበር የተክሌን ዝማሜ ከጎንደሬ ጋር ይደባልቁ ነበር፡፡ የዚህን ግጭት ምክንያት በጥልቀት ያስተዋሉት ራስ ጉግሳም አለቃ መኮነንን የደብሩ አለቃ ፣ አለቃ ብሬን የማህሌቱ አለቃ አድርገው ሾሟቸው ይላል (ፈለገ አዕምሮ፣ 1983፡9)፡፡

ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

> በአለቃ ታምራት ወንድሙ ገና በተማሪነታቸው ‹‹ዝኩ ካልዕ ረድዕ ዘያፈቅሮ ኢየሱስ ›› (ኢየሱስ የሚወደው ሁለተኛ አገልጋይ) የሚል ራዕይ የተነገረላቸው አለቃ ብሬ ናቸው፡ ፡ ….አለቃ መኮነን ግን ተክሌ በሞተ ጊዜ ጎንደሬ አቋቋን ተምረው ስለነበር ሁለቱን መደባለቅ ጀመሩ በዚህ ጊዜ አለቃ ብሬና አለቃ መኮነን ተጋጩ፡፡ ይህን የተረዱት ጉግሳም አለቃ ብሬን የማህሌቱ ሊቅ አደረጓቸው፡፡ አለቃ ብሬም ጥርት ባለው የተክሌ አቋቋም ትምህርታቸው ‹‹የነጭ ተክሌ ባለቤት ›› እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ ይህን ብቸኛ የተክሌ አቋቋም የቤት ቀለም ተክሌ ባስተማሩበት ጉባኤ ለብዙ ዓመታት አስተማሩ ፡፡ አለቃ መኮነንም በዚህ ጊዜ ከደብር አለቃነት አልፈው ወንበር ዘርገተው ተክሌ አቋቋምን አስተምረዋል (ቃመ.ቀኝ ጌታ አዳነ፣03/09/2010)፡፡

‹‹የአለቃ ተክሌን ትምህርት ከማንም ሳይደባለቅ በትክክል የተማሩ አለቃ ብሬ ናቸው፡፡ አለቃ ተክሌ እንደሚሞት በራዕይ ሲነገረው ትምህርቱን በትክክል ለትውልድ ያስተላልፋሉ ተብለው ከተመረጡ ሊቃውንት ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡ አለቃ ብሬም የተክሌ አቋቋምን ጥርት አድርገው ስላወቁ እና ስላስተማሩ የነጭ ተክሌ ባለቤት ይባሉ ነበር›› (ቃመ.መላከታቦር ኃይለ ኢየሱስ፣21/07/2010)፡፡ ‹‹አለቃ ቀለመወረቅ ከአለቃ ብሬ እና ከአለቃ መኮንን ከሁለቱም የተክሌን አቋቋምን የተማሩ ምሁር ናቸው ፡፡ራስ ጉግሳም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሊቃውንቱን ሲያማክሩ የተማሩ ሊቅ አለቃ ቀለመወርቅ እንዳሉ ይጠቆማሉ ራስ ጉግሳም በዚህ መረጃ መሰረት ቀለመወረቅን ወንበር ዘርግተው እንዲያስተምሩ አደረጉ›› (ቃመ.ቀኝ ጌታ አዳነ፣03/09/2010)፡ ፡

> አለቃ ቀለመወርቅ በመንበረ ብርሃን መምህር እንዲሆኑ በራስ ጉግሳ ቢታዘዙም ለወረታ ጊዮርጊስ አስተዳዳሪ ሆነው ነበር እንዲሁም አዲስ አበባ የአራዳ ጊዮርጊስ አስተዳዳሪም ነበሩ፡፡ በመጨረሻም የህሩይ ጊዮርጊስ አስተዳዳሪ ሆነው ሰርተዋል፡፡በእነዚህ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ እያለም ተክሌ አቋቋምን ያስተምሩ ነበር፡፡ እንዲያውም አለቃ ማህተም ጌጡ ከደብረ ታቦር ወረታ ባለው የእግር ጉዞ ከአለቃ ቀለመወርቅ ጋር እየተዘዋዋሩ ተምረዋል፡፡ በኋላም የእርጅናቸው ወራት ደርሶ ደብረ ታቦር ኢየሱስ እስኪመጡ ድርስ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ተክሌ አቋቋም ትምህርት ተቋርጦ ነበር፡፡(ቃመ.ርዕሰ መምህራን መርሻ፣08/09/2010)

‹‹አለቃ ቀለመወርቅም ይማም መምህር ከሆኑ በኋላም ይትባረክ የተባሉ ቄስ ልጃቸውን ባዩሽን በራስ ጉግሳ አማካኝነት ለአለቃ ቀለመወርቅ አጭተው አጋቧት፡፡ባዩሽም አለቃ ቀለመወርቅ አዲስ አበባ ወረታ በሚሄዱበት ጊዜ ህሩይ ጊዎርጊስን ታስተዳድር ስለነበረ አለቃ ባዩሽ ተብላለች›› (ቃመ.አባ ቢረሳው 25/08/10)፡፡


> አለቃ ቀለመወርቅ በእርጅና ዘመናቸው በደብረ ታቦር ኢየሱስ ወንበር ዘርግተው ብዙ ሊቃውንትን አስተምረዋል እነዚህም፡፡አለቃ ማህተም ጌጡን፣ መላከ ታቦር ልብሰወርቅ ወርቁን መሪ ጌታ እንደስራቸውን አስተምረዋል፡፡አለቃ ቀለመወርቅ የደብረ ታቦር ማህሌት አለቃ

በነበሩበት ጊዜ ለወረታም አስተዳዳሪ ነበሩ። አለቃ ማህተመም ለተክሌ አቋቋም በነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት ይማሩት የነበረውን የድጓ ትምህርት ትተው ከደብረ ታቦር እስከ ወረታ ባለው እግር ጉዞ ከአለቃ ቀለመወርቅ ጋር በመንገድ እየሄዱ ይማሩ ነበር።አለቃ ማህተምም በአለቃ ቀለመወርቅ እግር ተተክተው አስተምረዋል (ቃመ. ቀኛ ጌታ አዳነ፣03/09/2010)።



የአለቃ ቀለመወርቅ ይማም ፎቶ ፍሬ ማህሌት መጽሐፍ ላይ የተገኘ

የተክሌ አቋቋም ትምህርት በአለቃ ማህተም ጌጡ ዘመን ወደ እናቲቱ ማሪያም ተዛውሮ ነበር ይህም የሆነበት ምክንያት በወቅቱ ሌላ የተማረ እና በደብረ ታቦር ኢየሱስ ሊያስተምር የሚችል ሰው ስላልነበረ ነው (ቃመ. አባ ቢረሳው፣ 25/08/2010)።



የአለቃ ማህተም ጌጡ ፎቶ ከፍሬ ማህሌት መጽሀፍ የተገኘ

አለቃ ተክሌም ወደ ደብረ ታቦር ሄዱና በዚያው ወንበር ዘርግተው ማስተማር ቀጠሉ ብዙ መምህራንንም

አስተማሩ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የደብረ ታቦር ኢየሱስ ደብር እስካሁን ድረስ የተክሌ አቋቋም ጉባኤ ምስክር ሆኖ ያገለግላል ፡፡ የተክሌ አቋቋም መምህራን ሀረግ አወራረድ እንደሚከተለው ነው፡፡

| የመምህሩ ስም | የተማሪው ስም |
|---|---|
| አለቃ ገብረሐና | ተክሌ ገብረሐናን |
| አለቃ ተክሌ | መኮንንና ሌሎችን |
| አለቃ መኮነን | ቀለመወርቅና ሌሎችን |
| አለቃ ቀለመወርቅ | ማህተምን ሌሎችን |
| አለቃ ማህተም | መርሻን አስተምረዋል፡፡ ርዕሰ መምህራን መርሻ በአሁኑ ሰዓት በደብረ ታቦር ኢየሱስ እያስተማሩ የሚገኙ ናቸው፡፡ (የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤተ/ያን የ2000 ዓመት ታሪክ፣2000) |

ከእነዚህ መረጃዎች እንደምንረዳው ለተክሌ አቋቋም መካከለኛው ዘመንም ዋናው ወርቃማ ዘመን ነው ፡ ፡ አለቃ ብሬና አለቃ መኮነን ሁለት ወንበር ዘርግተው ማስተማራቸውም የትምህርቱን መስፋፋት ያሳያል፡ ፡ ራስጉግሳም ተክሌ በራሱ ቀለም ሳይበረዝ እንዲቀጥል ያደረጉትን ጥረት ስናይ እና  በአጠቃላይ እውቀት እንዲስፋፋ ከማህበረሰቡ ጀምሮ እስከ ንጉሡ እንዲሁም ሊቃውንቱ  ለአቋቋሙ የነበራቸው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑን፤ ማህበረሰቡ ተማሪዎችን ምግብ መጠለያ ወጭ ሸፍነው ማስተማራቸውና ትምህርት ሲጨርሱም ቦታው ያለ አስተማሪ እንዳይቀር በትዳር በመያዝ ያደረጉት ጥረት፤ንጉሡ በደብረ ታቦር  ኢየሱስ የሚደምቀው ማህሌት እናቲቱ ማሪያም እንዲደምቅ ያደረጉት ጥረት፤ ለመምህራን የሚያደርጉት እንክብካቤ ፤ ሊቃውንቱ ለተክሌ አቋቋም የነበራቸው ልዩ ፍላጎት ምዕራፉን ድጓውን ትተው ተክሌ አቋቋምን በእግር ከደብረ ታቦር ወረታ እየተመላለሱ የከፈሉትን መስዋዕትነት ስናይ በርግጥም ዘመኑ ለተክሌ አቋቋም ወርቃማ ዘመን ነው ለማለት ያስችላል፡፡  ከዚህ ቀጥሎ የአሁኑ ዘመን ብለን የምናየው አሁን በተክሌ አቋቋም ትምህርት ቤት ላይ እያስተማሩ ካሉት ርዕሰ መምህራን መርሻ መብራቱ ማስተማር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ  ያለውን ዘመን ነው፡፡

### 3.3.1. የተክሌ አቋቋም አሁን ያለበት ሁኔታ

ተክሌ አቋቋም በየዘመናቱ የነበረውን ታሪክ ስናይ የተስፋፋበት ወረቃማ ዘመን እንደነበረ ለምሳሌ ተክሌ በደብረታቦር ኢየሱስ ማስተማር እንደጀመረና ከእርሱ በኋላም በተተኩት እንደ አለቃ ብሬ የመሳሰሉ መምህራን ባስተማሩበት ዘመን በእጅጉ ተስፋፍቶ ነበር፡፡ በአንጻሩ አለቃ ገብረሐና ለጎንደር ሊቃውንት ሲያስተዋውቁት ተቀባይነት ማጣታቸው፣ ልጃቸው ተክሌም በማስፋፋት ላይ እንዳሉ መታመማቸውን ስናይ በየዘመናቱ የመጥፋት አደጋ ተጋርጦበት በሊቃውንት ጥበብ ከዘመናችን መድረሱን እንረዳለን፡፡ ይኸውም አለቃ ገብረሐና ተክሌን ደብቀው ማስተማራቸው፣ ካስተማሩ በኋላ በድርቡሽ እንዳይገደል ወሎ መላካቸው፣ ተክሌም አንደሚሞት ሲረዳ ለሶስት ሰዎች ትምህርቱን ከፋፍሎ በማስተማር እርስ በእርሳቸው ተማሪና መምህር ሆነው አንዲያውቁት እና እንዲያስተላልፉት ያደረገበትን መንገድ ስናይ ለተክሌ አቋቋም ዘመን ተሸጋሪነት የሊቃውንቱን ስልት እንረዳለን፡፡ በአሁኑ ዘመንም የተክሌ አቋቋም ይህ ችግር ተጋርጦበታል፡፡

ይህን አስመልክቶ ርዕሰ መምህራን መርሻ ፦ አለቃ ማኅተም በ1991 ጥር 10 ቀን እንደሞቱ በ1991 ሚያዚያ 20 ቀን አቡነ ኤልሳና ሊቃውንቱ ጉባኤ አድርገው ማኅተሙን ሰጡኝ፡፡ የተክሌ አቋቋምን በ1991

በነሐሴ አምስት ተማሪዎችን ይዤ እነ መላከታቦር ተሾመ ዘሪሁን ተክሌ አቋቋም ከዚህ በፊት በሚሰጥበት በደብረ ታቦር ኢየሱስ ትምህርቱ እንዲሰጥ ባደረጉት መሰረት ትምህርቱ ከመንበረ ብርሃን እናቲቱ ማሪያም ወደ ደብረ ታቦር ኢየሱስ መጥቶ እስካሁን በዚሁ እያስተማርኩ እገኛለሁ (ቃመ. 23/12/2010) በማለት ይገልጻሉ፡፡

መርሻ መብራቱ ማስተማር ከጀመሩበት ጀምሮ ከፍተኛው የተማሪ ቁጥር 30 ዝቀተኛው 7 ሲሆን በአሁኑ ሰዓት 15 ተማሪዎች በትምህርት ላይ ይገኛሉ፡፡ ተክሌ አቋቋም ከሌላው ጉባኤ ቤት አንጻር ሲታይ ተማሪው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ተማሪዎች የተክሌ አቋቋም ቶሎ በቀላሉ የማይያዝ ብዙ ጊዜ የሚጨርስ በመሆኑ ተማሪዎች ቶሎ ወደሚጨረስ አቋቋም ስለሚያዘነብሉ ፤ ቢማሩ እንኳን በሌላ አካባቢ የተክሌ አቋቋም ትምህርት ስለማይሰጥ ቅጥር አያገኙም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ትምህርት ቤቱ ውሃ፣ መብራት፣ሽንት ቤት የለውም የተማሪዎች ማደሪያ አሁን ላሉት ተማሪዎች በቂ ቢሆንም ሌላ ተማሪ ከተጨመረ ግን በቂ አይደለም እድሳትም ያስፈልገዋል (ቃመ.አንተነህ፣ 23/12/2010) ተክሌ እንዲዳከም ያደረገው ሌላው ምክንያት ለደብረ ታቦር ኢየሱስ የተክሌ አቋቋም ትምህርት ቤት ምንጭ ትምህርት ቤት የለውም ምንጭ የሌለው ጉባኤ ቤት ደግሞ ተማሪ ቁጥሩ ሊጨምር አይችልም (ቃመ.ርዕሰ መምህራን መርሻ፣ 23/12/07)



ርዕሰ መምህራን መርሻ መብራቱ የአሁኑ ደብረ ታቦር ኢየሱስ የተክሌ አቋቋም መምህር (ፎቶ 23/10/2010)

የተክሌ አቋቋም ሁሉም ተማሪ ለመማር አይደፍረውም፡፡ በዚህ ምክንያት ከሌላው ጉባኤ ቤት በባሰ በመጥፋት ላይ ነው፡፡ ቤተ ማርያም ጸናጽሉን ኀንደሬ ዘንጉን ተክሌ አድርገው በማደባለቅ አውጥተውታል፡፡ ይህ ለተማሪዎች ቀላልና ምቹ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ትክክለኛ የተክሌን እውቀት ለማሸጋገር ተማሪዎች ነጭ ተክሌ መማርና የተክሌን ታሪክ መጠበቅ አለባቸው (ቃመ.ቀኝ ጌታ አዳነ፣03/09/2010)፡፡

የተክሌ አቋቋም እግዚአብሔር ከሚመሰገንባቸው የቤተክርስቲኒቱ ስርዓት ውስጥ አንዱ ሲሆን በደብረ ታቦር ኢየሱስ ለረጅም ዘመናት ቤተ ክርስቲያኒቱ ስታገለግልበት ቆይታለች፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው

ከጀማሪው አለቃ ተክሌ ጀምሮ እስከ መላከታቦር ልብሰ ወርቅ ወርቁ ድርስ በደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተክርስቲያን በሁለቱም ማህሌት ሌላ አቋቋም ተቁሞ አይታወቅም። እንዲያውም ከደብረ ታቦር ኢየሱስ አልፎ የህዳር ሚካኤልና የሰኔ ሚካኤል ጸጉር ሚካኤል፣የግንቦት ልደታና የአስተርዮ ማሪያም መንበረ ብርሃን ማሪያም፣የህዳር ጽዮን መንበረ ንግሥት ማሪያም ሊቃውንቱ እየተዘዋወሩ በተክሌ አቋቋም ያገለግሉ ነበር። በአሁኑ ሰዓት በሚያሳዝን ሁኔታ በመጥፋት ላይ ነው ።ለዚህም ምክንያቱ የተክሌ አቋቋም ከሌሎች አቋቋም በበለጠ የጠነከረ በመሆኑ ተማሪዎች ለማማር አይደፍሩትም እንዲያውም ይፈሩታል ።ከዚህ ጋር ተያይዞ እንዳይማሩት ያደረገው የተክሌ አቋቋም በመጽሐፍ ተጽፎ ያልተቀመጠ መሆኑ ነው፤ ተማሪው ዜማውን ለማገናዘብ የሚችልበት መጽሐፍ አለመኖሩ ሌላኛው ትልቅ ምክንያት ነው።ከዚህ በተጨማሪ የተክሌ አቋቋምን የተማረ ሊቅ ከጨረሰ በኂላ ቅጥር የለውም ለዚህ ምክንያቱ ተክሌ አቋቋም በሁሉም ቦታ የማይሰጥ በመሆኑ ነው።የጎንደር አቋቋም ስልት በጣም መስፋፋቱና ዚቅ፣ መደልዎ አልባብ፣ ዝክረ ቃል ተብሎ በመጽሐፍ መቀመጡ እና የመማር በማስተማር ሂደቱ ምቹ መሆኑ ተማሪው ወደ ጎንደሬ አቋቋም እንዲያዘነብል አድርጎታል (ቃመ.መላከ ታቦር ኃይለ ኢየሱስ፣21/12/2010)።

አንተነህ ደግሞ ‹‹የአብነት ተማሪ ቁጥር መቀነስ በሁሉም ጉባኤ ቤት አለ ነገር ግን የደብረ ታቦር ኢየሱስን የተክሌ አቋቋም ትምህርት ቤት ከሌሎቹ በባሰ ሁኔታ እንዲዳከም ያደረገው ትልቁ ምክንያት መጋቢ (ምንጭ) ሌላ ትምህርት ቤት የሌለው መሆኑ ነው››።ይላል (ቃመ. አንተነህ፣07/10/2010)

ከእነዚህ መረጃዎች እንደምንረዳው የተክሌ አቋቋም የተዳከመባቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ይጠቃለላሉ፡ ፡

- የተክሌ አቋቋም ትምህርት ከሌሎች አቋቋም ትምህርቶች የበለጠ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ተማሪዎች ከጊዜ አንጻር የማይመርጡት መሆኑ፤
- የተክሌ አቋቋም የትምህርት ሂደት (ይትበሀል) በመጽሐፍ ተጽፎ ያልተቀመጠ በመሆኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹና ቀላል አለመሆን፤
- የተክሌ አቋቋም ክወኔ በዶክመንታሪ ፊልም ተቀርጾ አለመቀመጡ፤
- ለተክሌ አቋቋም ምስክር ጉባኤ ቤት ሌላ መጋቢ የባህላዊ ትምህርት ቤቶች አለመኖር፤
- የተክሌ አቋቋም ሊቃውንት ተምረው ከጨረሱ በኂላ ቅጥር አለመኖር፤
- ጉባኤ ቤቱ ለተማሪዎች የምግብ፣የውሃ፣ የልብስ እና የመብራት ፍላጎቶችን ያላሟላ መሆን፤
- የተክሌ አቋቋምን ትምህርት የአካባቢው ኅብረተሰብእ በቅርስነት አለመጠበቁ እንዲሁም
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ለአቋቋም ትምህርቱ አስፈላጊውን ትኩረት አለመስጠታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው።

## 3.4. የተክሌ አቋቋም ፋይዳ

እንደ ባስኮም ገለጻ የፎክሎር ጥናት የፎክሎር ተግባሩ (ፋይዳው) ላይ ማተኮር አለበት። ማንኛውም ፎክሎር ግለሰባዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም ኅብረተሰባዊ አገልግሎት ወይም ተግባር አለው። የአንድ ማህበረሰብ ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጠው ባህላዊ፣ማህበራዊ፣ ፓለቲካዊ እና ሥነ ልቡናዊ ተግባር አለ:: ይህ ተግባር

ስነልቡናዊ ውህደትን መፍጠር ማህበራዊ ትስስርን ማዳበር እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት ነው፡፡ ስለዚህ ፎክሎርን ዋና ተግባር ማስተማር፣ ማምለጥ፣ መግታትና መቆጣጠር፣ ማጠናከርና መትከል መግለጥ በሚሉት ይጠቃለላል፡፡ ከዚህ የተነሳ ቃል ታሪክ ባህልን አጽንቶ ለማቆየትና ማህበራዊ እሴትን ለማስቀጠል በማስተማር ተግባሩና በቅርስነቱ ለልማት ይጠቀማል፡፡ በዚህ መሰረት የተለያዩ የስነቃል ዘርፎች ለተለያየ አገልግሎት ይውላሉ፡፡ለምሳሌ እንቆቅልሾች የህጻናትን አእምሮ ለማስላት፤ምሳሌአዊ ንግግሮች የዳኝነት ስራን ለማቀላጠፍ፤ ሚቶች እና ተረቶች ተፈጥሮን ለማስተማሪያነት፣ ባህሪን ለመግራት፣ ወግ ልማድን ለማጠናከር፤ ምጸታዊ መዝሙሮችና ዘፈኖች ድብቅ ጥላቻን ለመግለጥና ለመዝራት ያገለግላሉ፡፡ ተክሌ አቋቋምም ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ ብዙ ነው፡፡ ይኸውም በተለያዩ ዐበይት በዓላት ሲቀርብ የተመልካችን ትኩረት ስለሚስብ የቱሪስት መስእብ በመሆን ለአካባቢው ብሎም ለሀገሪቱ ገቢ በማስገኘት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ይኖረዋል፣ የተክሌ አቋቋም በሚከወንበት ጊዜ ለሚታደሙ ሰዎች በግንኙነታቸው ተከባብረው ተወያይተው ተረዳድተው የተለያዩ በዓላትን እንዲያከብሩ ስለሚያደረግ አንድነታቸውን በማጠናከር ረገድ ማኅበራዊ ፋይዳ አለው፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት በዝርዝር የምናየው የተክሌ አቋቋምን ስነ ልቡናዊ እና ባህላዊ ፋይዳ የሚለውን ነው፡፡

## 3.4.1. ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ

በዚህ ጥናት ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ ሲባል ተክሌ አቋቋም ሲከወን ከዋኙና ታዳሚው የሚያገኙትን ደስታ፣ እርካታ፣ፌስታ ለማሳየት ነው፡፡የተክሌ አቋቋም በሚከወንበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ቃል ታሪኮችንም በመመርመር ያለውን ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ ከላይ በ 3.1. በአረፈ አይኔ (1979)፣በዳንኤል (2009) ፣ በፍሬ ማህሌት (1989) እንዲሁም በመላከ ታቦር ኃይለ ኢየሱስ ቃለ መጠይቅ ስለ ተክሌ አቋቋም ከተሰጡ ሀሳቦች በመነሳት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይኸውም ተክሌ ገብረሐና በወሎ አቋቋሙን ሲያቀርብ ህዝቡና ካህናቱ በአድናቆት መመለከታቸው፤ራስ ጉግሳ ከወሎ ወደ ደብረ ታቦር ካመጡት በኋላ ራስ ጉግሳ እና ህዝቡ ክዋኔውን ሲመለከቱ ‹በእውነት ይህስ ከመላዕክት የተገኘ ነው› እያሉ ማድነቃቸው፤ራስ ጉግሳም ወደ ኢየሩሳሌም ከተክሌ ጋር በመሄድ ተክሌ አቋቋምን እንዲያቀርብላቸው ከጠየቁ በኋላ ሲያቀርብላቸው በደስታ አለቀሱ ወዘተ. የሚሉት ትርክቶች የሚያሳዩት ይህንኑ ሥልቡናዊ ደስታ ነው፡፡ በተጨማሪም ከምልከታና ከቃለ መጠየቅ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ የልደት ታህሳስ 29 ‹‹ ቤዛ ኩሉ››፣መጋቢት 29 ‹‹ቀዳሚ ቃል›› የእርገት ‹‹ህይንተ ዕዝል›› በደብረ ታቦር ከተማ ነሐሴ 3 በቴዎድሮስ አዳራሽ የቅኔ ምሽት ላይ በቀረበው የተክሌ አቋቋም፣ የደብረ ታቦር ነሐሴ 13 ‹‹መንክረ ከሰተ›› በዐቢይ ጾም ደግሞ ከበሮም ጸናጽልም አገለግሎት ላይ ስለማይውሉ በተክሌ ዘንግ ብቻ ማህሌት ተቁሟል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ክዋኔዎች ማኅበረሰቡ ሃይማኖታዊ አለባበሱን ጠብቆ ቁሳዊ ባህሉን ይዞ በደስታ ይታደማል፡፡ በደስታ ይታደማል ሲባል ከዋኝና ከፊል ተሳታፊ ያላቸውን መስተጋብር የፊት ገጽታ አከዋወን በመመልከት የተረዳሁትን ነው፡፡ በቃል መጠይቅም በተለይ መላከታቦርና መሪጌታ ቀለመ ወርቅ ተክሌ አቋቋምን ሲገልጹ ተክሌ አቋቋም በተለይ የዘንጉ አጣጣል ልብን ደስ የሚያሰኝ ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ መረጃዎች የሚያመለክቱት ሥነ ልቡናዊ ፋይዳውን ነው፡፡

እንደሚታወቀው አንድ ማኅበረሰብ እምነታዊ ፣ መንፈሳዊ፣ ሃማኖታዊ ጉዳዮችን ሲከወን የሚያገኘው ሥነ ልቡናዊ ደስታ የጎላ ነው፡፡ የሚከወንበት ምክንያትም ለሚያምንበት ነገር አስፈላጊውን በማድረግ መንፈሳዊ እርካታና ጽድቅ ለማግኘት ነው፡፡ ከእነዚህ መረጃዎች እንደምንረዳው ተክሌ አቋቋም ዝማሜም በሚቀርብበት ጊዜ ሰዎችን በተመስጦ የሚይዝ፤በደስታ ከመመሰጣቸው የተነሳ የሚያስለቅስ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ከንጉሥ እስከ ተራ ማኅበረሰብ በመገረም የሚመለከተው፤ ከመገረማቸው የተነሳ ከመላዕክት የተገኘ ታምራዊ ዝማሜ የሚል ስያሜ እንደሰጡት እንረዳለን፡፡ ስለሆነም ለሃይማኖቱ ተከታዮችም ሆነ አቋቋሙ ሲቀርብ ለሚመለከቱ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ስነ ልቡናዊ ፌስታ የማስገኘት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ከሰነድ፣ ከምልከታና ከቃለመጠየቅ የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

### 3.4.2. የተክሌ አቋቋም ባህላዊ ፋይዳ

ባህል የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በጣም ሰፊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የምንመለከተው ኢትዮጵያ ካሏት የሚዳሰሱና የማይዳሳሱ ልማዳዊ እውቀት ካረፈባቸው ቅርሶቿ ውስጥ አንዱ ስለሆነው የተክሌ አቋቋም የማይዳሰስ ቅርስ ባህላዊ ጠቀሜታ ነው፡፡ ተክሌ አቋቋም ከላይ እንዳየነው እውቀቱ (መደበኛ ባልሆነው የትምህርት ስርዐት) ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ቅርስ ነው፡፡ በተለይ ክዋኔው ካህናት ሀገረሰባዊ ልብስ ለብሰው፣ በጸናጽል፣ በመቋሚያ፣በከበሮ፣ በተለካ ድምጽ፣ በመላ ሰውነታቸው የተክሌ አቋቋምን (ዝማሜ) ያቀርባሉ፡፡ የሃይማኖቱ ተከታዮችም ሀገረሰባዊ ልብስ ለብሰው በጭብጨባ ይሳተፋሉ፡ ፡ ስለዚህ ተክሌ አቋቋም በዜማ (ሙዚቃ)፣ በእንቅስቃሴ(ዳንስ)፣ እና ትዕይንት (ድራማ) መልክ ስለሚቀርብ ኢትዮጵያ ካሏት ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ቅርስ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ ክዋኔ ሳይቋረጥ መተግበር ባህልን ለመግለጽ፣ማኅበረሰቡ መከተል ያለበትን ሃይማኖታዊ እሴት ለማስተማር ባህልን ጠብቆ በማቆየት ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ ስለሚረዳ ባህላዊ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ ባህሉን፣ ማንነቱን የሚያውቅና የሚከውን ማኅበረሰብ በራሱ የሚተማመን መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ በአንጻሩ የራሱን ባህል የማያውቅ የማይከውን በራሱ የማይተማመንና በመጤ ባህል ጥገኛ የሚሆን ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ተክሌ አቋቋም መከወኑ ለሃይማኖቱ ተከታዮች የሚያበርከተው በራስ ባህል መተማመን ፋይዳ አለ፡፡ ስለተክሌ አቋቋም ማኅበረሰቡ እንዴት በማን እንደተደረሰ፣ በዘመናት ታሪኩ ምን እንዲመስል በሥነ ቃል መተረኩ፤ በሚከወን ጊዜ በዜማ በውዝዋዜ በትዕይንት መቅረቡ ፤ በሚቀርብበት ጊዜ ካህናትና ምእመናን ባህላዊ ልብሶችን ለብሰው መሆኑ፣ መቋሚያ፣ጸናጽል፣ ከበሮ ወዘተ ቁሳዊ ባህሎች መኖራቸው እንዲሁም የሃማኖቱ ተከታዮች ክዋኔውን በመከወናቸው መንፈሳዊ እርካታ ማግኘታቸው የተክሌ አቋቋም ብቻ ሳይሆን የዘረዘርናቸው ሌሎች ባህሎችም እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የተክሌ አቋቋም መከወንና መጠበቅ ሥነቃል ፣ሀገረሰባዊ ትውን ጥባባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባህል (ሁሉም ባህሎች) አንድ ላይ እንዲከወኑ ስለሚያደርግ ባህላዊ ፋይዳው የጎላ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 3.5. የተክሌ አቋቋምን ወደ ታሪኩ ለመመለስ ምን መደረግ አለበት

ከመረጃዎች እንደምንረዳው የተክሌ አቋቋም በተለያዩ ምክንያቶች በአሁን ሰዓት በመጥፋት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የደብረ ታቦር ኢየሱስና ቅድስት ስላሴ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ የደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት እና የሚመለከታቸው አካላት የተክሌ ሊቃውንትን በያሉበት ፈልገው በመጽሐፍ ቢያሳትሙት፤የተክሌ አቋቋም ክዋኔውን በምስል (በዶክመንታሪ ፊልም) ቀርጾ ለሚቀጥለው ትውልድ ቢተላለፍ፣ የተክሌ አቋቋምን የመማር ማስተማር ሂደት ምቹና ቀላል ከማድረጉም ባሻገር የተክሌ አቋቋም ይትበሀል ሳይበርዝ ቅርስነቱ እንደተጠበቀ ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚረዳ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡የተክሌ አቋቋም መጋቢ (ምንጭ) ትምህር ቤት የሌለው ነው ፡፡ ስለሆነም ጥናቱ የተክሌ አቋቋሙ ያለበት ሁኔታ በዋናነት የሚመለከተው ደብረ ታቦር ኢየሱስና ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ከሀገረ ስብከቱ ከህብረተሰቡ ጋር በመተባበር በደብረ ታቦር ከተማ በሚገኙት ሰባት ቤተ ክርስቲያናት የተክሌ ሊቃውንትን በመመደብ ለደብረ ታቦር ኢየሱስ ጉባኤ ቤት ምንጭ መጋቢ እንዲሆኑት ቢያደርጉ፡፡የተክሌ አቋቋም በሁሉም ቦታ የማያስቀጥር መሆኑ ተጠቅሷል ስለሆነም ይህ የሆነበት ምክንያት ትምህርቱ በዘመናችን ባለመስፋፋቱ እና የዘመናችን ኢትዮጵያ ህዝብ ስለተክሌ አቋቋም ግንዛቤ የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የደብረ ታቦር ከተማ ባህልና ቱሪዝም፣የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም፣የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ፣የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ተክሌ አቋቋምን በማጥናት በመሰነድ ታሪካዊ፣ባህላዊ፣ሀገራዊ ጠቀሜታውን በማሳየት እና ግንዛቤ በመፍጠር ማኅበረሰቡ የኔ ሀብት ብለው እንዲጠብቁት ቢደረግ፡ደብረ ታቦር ኢየሱስ ከደብረ ታቦር ከተማ በቅርበት የሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ስለሆነም የደብረ ታቦር ከተማ መብራት ኃይል ውሃ ልማት ቢሮዎች ለዚህ ሃገራዊ ቅርስ የተክሌ አቋቋም ትምህርት ቤት መብራና ውሃ የማግኘት እድል ቢኖረው ለትምህርቱና ለክዋኔው አንድ ምቹ

ሁኔታን በመፍጠር ረገድ አስተዋኦ ይኖረዋል።

የሁሉም የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ማኅበረሰብን ማገልገል አንዱ አላማቸው እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህ ለተክሌ አቋቋም ቅርስ በቅርበት የሚገኘው የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ የተክሌ አቋቋምን እንዲጠና ቢያደርግ ይህ ጥናት ዘረፈብዙ ይዘትና ጠቀሜታ ላለው የተክሌ አቋቋም በቂ ነው ብየ አላስብም ለምሳሌ ከፎክሎር አንጻር የተክሌ አቋቋም አከዋወን ሂደት ብቻውን፣ እንዲሁም ጠቀሜታው ከሙዚቃ ከፈጠራ አንጻር ሊጠና ይችላል። በተጨማሪም ከዚህ ቃል ተረክ በመነሳት የ19ኛውን ክዘ/መን የኢትዮጵያ ታሪክ ማጥናት ይቻላል፡ ፡ ታሪኩን በመሰነድ ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ ቢፈጥር ከዚህ በተጨማሪ ይህን ቅርስ የሚማሩትን የተክሌ ተማሪዎች ከምግብ ጀምሮ የሚየስፈልገቸውን በሟማላት የበኩሉን ቢየደርግ መልካም ነው::

በዚህ ጥናት የተክሌ አቋቋም ቃላዊ ታሪክ (Oral History) እና ፋይዳውን ለማሳየት ተሞክሯል ። የተገኘው ውጤትም የተክሌ አቋቋም ትምህርት፡- በአለቃ ገብረ ሐና በጣና ሐይቅ አካባቢ እንደተደረሰ፤አለቃ ገብረሐና ለጎንደር ሊቃውንት አቋቋሙን ሲያስተምሩ ተቀባይነት እንዳጡና የመጨረሻ የመፍትሔ አማራጭ ልጃቸውን ተክሌ ገብረ ሐናን ቤት ዘግተው እንዳስተማሩ፣ ተክሌም ከአባቱ ያገኘውን ጥበብ ይዞ ወሎ እንደሄደ፤የተክሌ ሊቅነት በወሎ ተንታ ሚካኤል ሲመረቅ እንደተገለጸ፤ ሊቅነቱ ከታወቀ በኂላ ንጉሥ ራስ ጉግሳ ወሌ ከወሎው ንጉስ ራስ ሚካኤል ዘንድ አስፈቅደው ደብረታቦር ኢየሱስ እንዳመጡት ጥናቱ አትቷል።ጉግሳ ለተክሌ የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪነት እንዲሁም የተክሌ አቋቋምን የማስተማር ስልጣን አንድ ላይ እንደሰጡት ፤ተክሌም በደብረታቦር ኢየሱስ ሰፊ ጉባኤ ቤት ዘርግቶ እንዳሰተማረ እና በብዙ የኢትዮጵያ ክፍል የትምህርቱ ዝና ቢሰማም ብዙ ሳይቆይ እንደሞተ፤ እርሱ እንደሞተም በእርሱ ወንበር አለቃ መኮንን እንደተተኩ ተጠቁሟል። አለቃ መኮነን የጎንደሬን ትምህርት ከተክሌ ትምህርት ጋር በመደባለቃቸው ራስ ጉግሳ መኮንን የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ፤ አለቃ ብሬን የጉባኤው አለቃ አድርገው እንደሾሟቸው፤ከአለቃ ብሬ በኂላ አለቃ ቀለመወርቅ እንደተተኩ ፤ ከአለቃ ቀለመወርቅ አለቃ ማኀተም እንደተተኩ፤ከዚያም በአሁኑ ጊዜ በማስተማር ላይ ያሉት ርዕሰ መምህራን መርሻ መብራቱ አስተማሪነቱን እንደተረከቡ ጥናቱ ጠቁሟል። የተክሌ አቋቋም በአሁኑ ወቅት በመጥፋት ላይ እንደሆነ፤ለዚህም ምክንያት የሆኑ ችግሮች፡- የተክሌ አቋቋም በመጽሐፍ ተጽሕፎ ያልተቀመጠ በመሆኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹና ቀላል አለመሆኑን፤ክዋኔው በፊልም ተቀርጾ ያልተቀመጠ መሆኑ፤ለተክሌ አቋቋም ምስክር ጉባኤ ቤት መጋቢ (ምንጭ) የባህላዊ ትምህርት ቤቶች አለመኖር ዋና ዋና ችግሮች ናቸው። ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች የምግብ፣የመጠለያ፣ ፣ የውሃ እና የመብራት ፍላጎት ያላሟላ መሆን፤የተክሌ አቋቋምን ትምህርት የአካባቢው ኅብርተሰብ በቅርስነት አለመጠበቅ፤ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ለአቋቋም ትምህርቱ አስፈላጊውን ትኩረት አለመስጠታቸው፤ ትውልዱ በራሱ ይህን ሀገረሰባዊ ዕውቀት ችላ ማለቱን ጥናቱ አትቷል። ለዚህም መፍትሔ የሚሆኑ ሀሳቦችን፡-የተክሌ አቋቋምን ይትበሀል በመጽሐፍ በማሳታም የመማር ማስተማሩን ሂደት ምቹና ቀላል ማድረግ፣በደብረ ታቦር ከተማ ባሉ ቤተክርስቲያናት ለተክሌ አቋቋም ምንጭ የሚሆኑ ትምርት ቤቶች ማቋቋም፣የተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላት ፤የሚመለከታቸው አካላት ለተክሌ አቋቋም አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠትና በቅርስነት መጠበቅ የሚሉትን የመፍትሔ ሀሳቦች ጥናቱ ጠቁሟል ።ከዚህ በተጨማሪ ተክሌ አቋቋም ክዋኔ ሃይማኖታዊ ስነ ልቡናዊ ባህላዊ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል።

## ምስጋና

ይህ ጥናት እውን ይሆን ዘንድ መረጃ በማቀበል ለተባበሩኝ ባለሙያዎች በሙሉ ልባዊ ምስጋናየ በአሉበት ይደረሳቸው። ለመረጃ አቀባይ መላከ ታቦር ኃይለ ኢሱስ ፈንታሁን ፣ ቀኝ ጌታ አዳነ እንግዳ፣ አባ ቢረሳው፣ ርዕሰ መምህራን መርሻ መብራቱ፣መሪጌታ ዘውዱ እና ሌሎች ስማቸውን ያልጠቀስኳቸውን ሰዎች

ምስጋናየን አቀርባለሁ።በመቀጠልም ይህን ጥናት በመተቸት፣ በማረም ፣በማስተካከልና በመገምገም ሙያው እገዛ ያደረጉልኝ ምሁራን በሙሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናየ ይድረሳቸው።

## References

--.( 1992). "Oral Literature", *Journal of Ethiopian Languages*, Vol 2. Addis Ababa University.

Ayne Arafa Hagos. (1987). *Aleqa Gabra Hanna and His Hilarious Jokes*. Addis Ababa, Negd Publishing House.

Barbara, Alle. (1979).*The Personal Point of View in Orally Communicated History: Western States Folklore Society*, Jstor Press.

Bascom, William. (2007). Four Function of Folklore: *the Journal of American Folklore,*Jstor press.

Dabra Tabor City Administration (ND). *The Historical Dabra Tabor on the Road to Re-development*. Bahir Dar, Galaxy Publishing and Advisement.

Dorson, Richard M. (1972). *Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago*: The University of Chicago Press.

Fekade Azeze. (1999). *The Guide to Oral Literature*. Addis Ababa, Bole Publishing House,\

Henok Wolde Mika'el. (1998). *Medalwo Albab*. Addis Ababa, Addis Ababa Publishing House Mesele Lemma. (2014). *Liqu (The Scholar) Aleqa Gebra Hanna*. Addis Ababa, ZA Publishing House.

No name. (1991). *Falaga Aemero*. Dabra Tabor Publishing House.

Propp, Vladmir. (1984). *Theory and History of Folklore*. Translated by Ariadna Y. Martin and Richard P. Martin Edited by Anatony Liberman. Minneapolis: University of Minnesota Press. www.danielkibret.com

Solomon Teshome. (2015). *Folklore: What it is and the Research's Focus*. Addis Ababa, Far East Publishing House.

Ti'ume Lesan. (1989). *Yared and his Hymns*. Addis Ababa, Addis Ababa Publishing House.

Yalew Endaweqe. (2005). *The Basic Rules and Conducts of Research*. Bahir Dar University, Alfa Publishers.

Zerihun Asfaw. (2000). *The Basics of Literature*. Addis Ababa, Addis Ababa University Press.